የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# በፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ

# የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ

# የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

ጥር /2012 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## በፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ

## የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ

## የ2011 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት

የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ የተመደበለትን መደበኛ በጀት በፋይናንስ አዋጅ፣ ደንብ እና በተከታታይ በወጡ መመሪያዎች መሠረት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሃብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ ከዚህ ሪፖርት ጋር የተያያዙትን የ2011 በጀት ዓመት የሂሣብ ሪፖርቶች እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶቹን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኤጀንሲው ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶቹን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን መሠረት በማድረግና የዋና ኦዲተርን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው፡፡እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ/የኦዲት አስተያየት/ ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ኤጀንሲው ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በኤጀንሲው ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተለው የኤጀንሲው የተጠቃለለ የሂሳብ ማመዛዘኛ ሪፖርት ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዞ ቀርቧል፡፡

- የተጠቃለለ የሂሳብ ማመዛዘኛ ሪፖርት

የኤጀንሲው የሂሣብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀትና በመንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል

የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪ እና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደርን አዋጅ ደንብና መመሪያ የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

**ገቢ**

1. በበጀት ዓመቱ የተሰበሰበ ገቢ ብር 17,109.60 ሪፖርት ሳይደረግ ተገኝቷል፡፡

**ወጪ**

2. የሚወገዱ ዕቃዎችን ዋጋ ለሚገምቱ ባለሙያዎች የአገልግሎት ክፍያ በሚል ብር 8,000.00 ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡
3. አገልግሎት ለማይሰጡ ስልኮችና ፋክስ ማሽኖች ብር 6,343.68 የኪራይ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
4. የመገጣጠሚያ ደብዳቤ ባለመቅረቡ አለአግባብ ብር 2,576.550 የውሎ አበል ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
5. አለአግባብ የተፈጸመ የውሎ አበል ክፍያ በድምሩ ብር 3,714.35 ተገኝቷል፡፡
6. የግዥ ዕቅድን በመተላለፍ 6,982 የታሸጉ ውሃዎች በዕቅድ ከተያዘው ውጪ በመግዛታቸው ምክንያት ብር 33,772.43 አለአግባብ የተከፈለ መሆኑ ታውቋል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 6 ከተገለጹት በስተቀር በእኛ አስተያየት የመ/ቤቱ የሂሣብ ሪፖርቶች በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2011 ዓ.ም የተሰበሰበውን ገቢ የተከፈለውን ወጪና የበጀት አጠቃቀሙን በአጥጋቢ ሁኔታ ያሣያሉ፡፡

**ሌሎች ጉዳዮች፤**

7. በኤጀንሲው የቀረበው የግዥ ዕቅድ በግዥ መመሪያው መሠረት የግዥ ዕቅድ ይዘትን ተከትሎ ያልተዘጋጀ መሆኑ ታውቋል፤

ከሠላምታ ጋር

------------------------

ትዕግሥት ረታ

የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች

ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

ቀን 28/05/2012